# የፀረ- ሽብር ህጉ የሚያስፈራው ህገ-ወጦችን ብቻ ነው!

**መሐሪ ይፍጦር**

yiftermehari@gmail.com

በዕድገት ማማ መሰላል ላይ እየወጣ የሚገኝ ሀገርና ህዝብ የጀመራቸው የልማትና የዴሞክራሲ ጉዞዎች እንዲቃኑለት የአስተማማኝ ሰላም መኖር ወሳኝነት አያጠያይቅም። ሰላም ከሌለ፤ ስለ ልማትም ሆነ ስለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባህል ግንባታ መናገሩ ከጉንጭ አልፋነት የዘለለ ትርጉም አይኖረውም፡፡ ለምን ቢባል በዚያች ሀገር ውስጥ ሰላም በአስተማማኝ ሁኔታ ካልተረጋገጠ፤ ሊመጣ የሚችል ዕድገትም ይሁን ስር እንዲሰድ የሚፈለግ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ከቶም ሊታሰብ ስለማይችል ነው፡፡

ከዚህ ጥቅል ነባራዊ ሁኔታ ተነስተን ጉዳዩን ወደ ሀገራችን ስንመልሰው፤ ኢትዮጵያ የጀመረችው የዕድገትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ባህል ግንባታ ሂደት ስኬታማ ሆኖ እንዲቀጥል፤ አስተማማኝ ሠላም የሰፈነበት ምህዳርን መፍጠር “ለነገ” የምትተወው ተግባር አይደለም፡፡ ለምን ቢባል፤ ለኢትዮጵያ ፈጣን ልማትን ማምጣትና ከተመፅዋችነት መላቀቅ “የሞት-ሽረት” ያህል የህልውና ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡ ታዲያ ሰላምን በማረጋገጥ ሂደት ውስጥ፤ ለብሔራዊ ደህንነቷ ስጋት የሆኑ እንቅስቃሴዎችን መከላከልና መቆጣጠር የግድ ይላታል፡፡

የሀገራችን የብሔራዊ ደህንነት ስጋቶች ናቸው ተብለው ከሚጠቀሱት ተግባሮች ውስጥ አንዱና ግንባር ቀደም ተጠቃሹ የሽብርተኝነት እንቅስቃሴ ነው፡፡ ሽብርተኝነት የራሱ መንስዔዎችና ዓላማዎች ቢኖሩትም፤ በውጤነት የሚያስከትለው አደጋ ግን ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን የሀገር ውስጥ አንዳንድ ሁከት ናፋቂ ተቃዋሚ ተብዬዎችና የውጭ አለቆቻቸው ተግባሩ የከፋ የሆነውን ይህን አደጋ እያወቁ ራሳቸውን ለመከላከልና ከተጠያቂነት ለመዳን ሲሉ ለህጉ የተጣመመ ትርጓሜ ቢሰጡትም፤ እውነታው ግን ሽብርተኝነት በየትኛውም የዓለም ክፍል ተቀባይነት የሌለው ህዝብ ጨራሽ ዘግናኝ የጭካኔ ተግባር መሆኑ ነው፡፡

ሀገራችን የሽብር ድርጊት ቀዳሚ ገፈት ቀማሽ መሆኗ ከማንም የሚሰወር አይመስለኝም። በቀድሞው የግብፅ ፕራዚዳንት ሆስኒ ሙባረክ ላይ አዲስ አበባ ውስጥ የተቃጣው የግድያ ሙከራ፣ የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትር በነበሩት በአብዱልመጂድ ሁሴን ላይ የተካሄደው የግድያ ሙከራ፣ በግዮንና ዋቢ ሸበሌ እንዲሁም በትግራይ ሆቴሎች ላይ የተፈፀሙት የቦምብ ጥቃቶች

ይህን ዕውነታ አመላካቾች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም በኤርትራ መንግስት አቀነባባሪነት በተለያዩ ጊዜያት አአሸባሪዎቹ ኦነግና ኦብነግ መልዕክት አድራሽነት አማካኝነት ሊፈፀሙ ታቅደው በህዝቡና በፀጥታ ሃይሎች ትብብር የከሸፉ የሽብር ሙከራዎች ይጠቀሳሉ። በዚህም ሳቢያ የኢትዮጵያ መንግሰት አደጋውን ለመከላከል ቁርጠኛ አቋም ወስዷል። ችግሩ የህግ ማዕቀፍ ተበጅቶለት እንዲቀረፍ ለማደረግ ጥረት እያደረገ ነው።

እርግጥ ሽብርተኝነት የዜጎችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የሚገታ፣ የመንግስትን የማስፈጸም አቅም የሚያዳክም ብሎም በሀገር ደረጃ የተጀመረውን የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን የሚያደናቅፍ አሊያም የሚያጓትት አሉታዊ ውጤት ያለው አፍራሽ ተግባር በመሆኑ መንግስት የወሰደው እርምጃ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ እናም በየጊዜው በሀገራችን ብሔራዊ ደህንነት ላይ የተቃጡ የሽብር ጉዳዮችንና ወደፊት ሊኖሩ በሚችሉ ስጋቶች ላይ ተንተርሶ የተያዘ ትክክለኛ አቋም ነው ማለት ይቻላል፡፡

መንግስት የሀገሪቱንና የህዝቡን ሁለንተናዊ ደህንነት የመጠበቅ እንዲሁም በዓለምና በአህጉር አቀፍ ደረጃ ከሽብርተኝነት አኳያ ያለበትን ኃላፊነትና ግዴታ ለመወጣት የፀረ - ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አውጥቷል፡፡

አዋጁ ምናልባትም በራሳቸው የማይተማመኑ አንዳንድ ተቃዋሚ ተብዬዎችና በየግል ሚዲያዎች ውስጥ የጋዜጠኝነት ካባን ደርበው የተወሸቁ ጥቂት ግለሰቦች እንዲሁም የውጭ አለቆቻቸው ከዓላማው ጋር ባልተገናኘ መልኩ “ህጉ የተቃዋሚዎችን እንቅስቃሴና የፕሬስ ነጻትን የሚያፍን ነው” የሚል ያልተገባ ስም እንደሚሰጡት ሳይሆን፤ ህዝቦች በሠላም፣ በነጻነትና በተረጋጋ ሁኔታ ያላቸው ህገ- መንግስታዊ መብት ከመሸርሸር አደጋ እንዲጠበቅ እንዲሁም ሽብርተኝነት ለሀገራችን ሁለንተናዊ ዕድገት ጸር በመሆኑ የህግ አግባብን ተከትሎ ተግባሩን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ያለመ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህን እኩይ ተግባር ፈጻሚዎችንና አስፈጻሚዎችን እንቅስቃሴ ከጅምሩ ለመቅጨት የአዋጁ አስፈላጊነት አያጠያይቅም፡፡

ግና እንደ አንድነት ፓርቲ ዓይነት አመራሮችና በጋዜጠኛ ስም የሚንቀሳቀሱ ጭፍን ተቃዋሚዎች ከራሳቸው ውስጣዊ ስጋት በመነሳት “የፀረ-ሽብርተኝነት ህጉ ይዘረዝ ወይም ይሻሻል” እንዲሁም “ህጉ ያስፈራል” የሚሉ አሉባልታዎችን በማናፈስ ለሽብርተኞች ድጋፍ ሲሰጡ ይስተዋላሉ። ይሁንና በእኔ እምነት የፀረ-ሽብር ህጉ የሚያስፈራው ህገ-ወጦችን ብቻ በመሆኑ አሉባልታው ስር ስለሌለው መታረም ይኖርበታል። የዚህ ፅሑፌ ዋነኛ ዓላማም ይህን ስህተት ማረቅ ነው።

ስለ ሽብርተኝነት ሲነሳ በመርበትበት የሚይዘውንና የሚጨብጠውን የሚያጣው አንድነት ፓርቲና አመራሮቹ ህጉ እንዲሰረዝ በደመ-ነፍስ የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ለዚህ አባባሌ አስረጅ ለማቅረብ ያህል፤ በቅርቡ የተከበሩ የፓርላማ አባልና የፓርቲው አመራር አቶ ግርማ ሰይፉ በዓይጋ ፎረም ድረ-ገፅ ላይ "ፀረ-ሽብር ህጉ ለምን አያስፈራ?" በሚል ርዕስ በሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ሃሳባቸውን ላሰፈሩ አንድ ፀሐፊ የሰጡትን እጅና እግር የሌለውን ምላሽ ጥቂቱ ነጥቦችን ወስዶ መመልከት ይቻላል–ህጉን ለማሰረዝ ስለተደረገው ጉዳይ፣ ህጉ ለምን እንደማስፈራ፣ የአሰራር ቅደም ተከቶሎችን…ወዘተ.በማንሳት። ታዲያ እዚህ ላይ የእኔ ዓላማ የሪፖርተሩን ፀሐፊ ወክዬ ምላሽ መስጠት አለመሆኑ ሊታወቅልኝ ይገባል። ፅሑፌም ከሪፖርተሩ ፀሐፊ ጋር ግንኙነት የለውም። ይሁንና አቶ ግርማ የአንድነት ፓርቲ አመራር በመሆናቸው በፀረ-ሽብር ህጉ ላይ የሰጡት ሃሳብ ፓርቲያቸውን የሚወክል ነው። እናም ሃሳቤ የፓርቲውን የተሳሳተ አቋም በማረም ላይ ያተኮረ ብቻ መሆኑ ግንዛቤ እንዲያዝልኝ እፈልጋለሁ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ አስገራሚ "የህጉ ይሰረዝ" ዲስኩር ስር በመስደድ ላይ ባለው በሀገሪቱ የዴሞክራሲ ሂደት ላይ ማፌዝ መሆኑ ከማንም የሚሰወር አይመስለኝም። ታዲያ ይህን ሰሞነኛ ኢ-ዴሞክራሲዊ ክስተትን ምን እንበለው?– 'ወቸው ጉድ!' ወይስ 'የፀረ- ዴሞክራሲያዊነት ዛር ከያዘ አይለቅም?'– ለእኔ ግርምታውን የወለደው የፀረ-ዴሞክራሲያዊነት አስተሳሰብ በመሆኑ ሁለቱም ልዩነት የላቸውም። እስቲ ለማንኛውም እየተገረምን ይህን ጉደኛ የአንድነትን የተለመደ 'አቧራው ጨሰ' ዓይነት ፀረ-ህገ-መንግስታዊ ተግባርን ወደ ኋላና ፊት መለስ ቀለስ እያልን እንመልከተው።

በእኔ እምነት አመራሮች ስልጣን እንደ እህል ውሃ እየራባቸውና እየጠማቸው ከፓርቲው ራሳቸውን እያገለሉ በየሚዲያው የቃላት አለንጋን በመምዘዝ እየተዥለጡ በሚገኙበት አሳዛኙ አንድነት ፓርቲ፤ ፊርማ ማሰባበብ የሚገባው ራሱ ከመፍረስ የሚያድነውን የአባላቱን ይሁንታ ለማግኘት በጣረ ነበር። ይሁንና በውስጡ ያለውን ሽኩቻ ለመሸፋፈን ህገ-መንግስቱን ለመርገጥ መሞከሩ ያው የተለመደውን የፖለቲካ አማተርነቱን ለመከወን ከመፈለጉ ውጪ ያሳየን ነገር የለም። እርግጥ እንደ ማንኛውም ሀገር በቀል ተቃዋሚ ፓርቲው 'ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን አክብሬ እንቀሳቀሳለሁ' በሚል በምርጫ ቦርድ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ነው። ግና ምን ያደርጋል!?–ልክ እንደ ሰሞኑ ዕውነተኛው ማንነቱ ድንገት እያፈነገጠበት ዴሞክራሲያዊውን ህገ-መንግስት ለመረጋገጥ እየከጀለ ተቸገረ እንጂ።

መቼም "የፀረ-ዴሞክራሲያዊነት ዛር አንዴ ከያዘ 'በሶስት ሰባት' ጠበል ጠመቃም እንኳን ቢሆን አይለቅም" የሚባለውን ሃቅ ለማረጋገጥ የፈለገ ሰው የአንድነትን የትናንትና የዛሬ ማነነትን ብቻ መመልከት በቂው ይመስለኛል። ምክንያቱም የፓርቲው አመራሮች 'አድሮ ቃሪያ' በሚሉት

ዓይነት አካሄድ እየተመሩ፣ ዛሬም ቢሆን መልሰው መላልሰው ውሃን እየወቀጡ እንቦጭ ሲያደርጉ ሊያገኛቸው ስለሚችል ነው።

ፀረ-ዴሞክራሲያዊነት ያለበትን ቦታ እያሸተቱ 'በድንኳን ሰባሪነት' መገኘት የማይሰለቻቸው የፓርቲው አመራሮች፤ አብዛኛዎቹ በምርጫ 97 ወቅት በቅንጅት ነውጠኛ አመራሮች ስር ታቅፈው 'ሁከት' የተሰኙን ፍቅረኛቸውን ለማግኘት ሲሉ የአደባባይ ላይ ነውጥን ቀምረው መንቀሳቀሳቸው የሚዘነጋ አይደለም። የወቅቱ ህልማቸው ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በአመፅ መናድ እንደነበር አምነው ምህረት እንዲደረግላቸው በጠየቁበት የይቅርታ ደብዳቤያቸው ላይ መግለፃቸውም እንዲሁ።

ታዲያ እንደ እኔ ዓይነት ተላላ ዜጋ 'በቃ እነዚህ ሰዎች ስክተታቸውን አምነዋል፣ እናም ፀረ-ዴሞክራሲያዊነታቸውን እርግፍ አድርገው ይተዋሉ' የሚል እሳቤ አድሮብን ነበር።...ልጄ እነርሱ ምን በወጣቸው?!...እንዴት ሲያደርጉ እንዲህ ዓይነቱን ሰናይ ተግባር ይፈፅማሉ?...ምን በወጣቸው!...ከዚህ ይልቅ አሮጌውን ማንነታቸውን እንደያዙ መድረክ የተሰኘ እምነት አልቦ የድንቡሽት ቤትን በመገንባት በአዲስ ማለያ ብቅ ማለትን ነው የመረጡት–አዳዲስ ተዋንያንን በማከል።...

...ግና በምርጫ 2002 ወቅትም የፀረ-ህገ-መንግስትነትን ካባ ደርበው የኢ-ዴሞክራሲያዊነት ተመሳሳይ ዜማን እያቀነቀኑ በመገኘታቸው፤ ሚዛናዊውና ፍትሐዊው የሀገራችን መራጭ ህዝብ አጠቃላይ እርስ በእርሱ የማይተማመነውን የቡድኑን ስብስብ ዳግም ወደ ፓርላማ ዝር እንዳይል በካርዱ ቀጥቷቸዋል። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ አንድነት የተሰኘው ፓርቲ 'ካልመራሁህ ሞቼ እገኛለሁ' የሚለው መድረክ የተሰኘውን የእሳትና ጭድ ስብስብ፤ 'ያለ እኔ ፈቃድ ልማትን፣ ሰላምንና ዴሞክራሲን ያጎናፀፈኝን ህገ- መንግስት ቀዳድዳችሁ ልትጥሉ እንዲሁም የእኔን ሉዓላዊ መብት በመግፋት በውጭ ሃይሎች አማካኝነት የስልጣን እርካብን ልትቆናጠጡ በየኤምባሲው አርቲ ቡርቲ ወረቀት ይዛችሁ ስትዞሩ ተመልክቻችኋለሁ' የሚል ነበር።...መቼም ለአንድ ለሚመዛዝን ወገን ከዚህ በላይ ውርደት ያለ አይመስለኝም። እውነትም አንድ የፖለቲካ ፓርቲ 'ይመርጠኛል' በሚለው ህዝብ እንዲህ ከመብጠልጠል በላይ ከቶ ሌላ ነገር ምን ይመጣበታል?–ምንም።

የአንድነት አመራሮች ግን ከዚህ ስህተታቸው ከመማር ይልቅ ያመሩት ወደ ሌላ ፀረ-ህገ-መንግስት ተግባር ነበር–የመካከለኛው ምስራቅና የሰሜን አፍሪካውን አብዮት በግድ ከኢትዮጵያ ጋር አጣብቀው በመስፋት ሀገራችን ውስጥ እንዲቀጣጠል በቀቢፀ-ተስፋ እየተመኙ ከህዝቡ ይሁንታ ውጪ በአቋራጭ ስልጣንን ለማግኘት መቋመጥ። ታዲያ ያ ወቅት አንድ አመፅ ሌላ ሀገር ውስጥ ሲቀሰቀስ የስሜት ህዋሳታቸው እንዳች ዕፅ የወሰዱ ያህል የሚነቃቃው የአንድነት ሰዎች፤ በጉዳዩ

ዙሪያ በአስገራሚ ሁኔታ ወደ 'ትንቢት ተናጋሪነት'ም ተቀይረው ነበር። እንዲያውም አንዳንድ ወገኖች የፓርቲውን አመራሮች የ8ኛው ሺ የከሰሩ መፅሐፍ ገላጮች እስከማለት ደርሰዋል።…

ያም ሆነ ይህ እስቲ ለቅምሻ ያህል የፓርቲውን አመራሮች ትንቢት ተናጋሪነት በጥቂቱም ቢሆን እንካችሁ ልበል።…ግና ከማን እንጀምር?...ለነገሩ ይህ ጉዳይ አያሳስበንም–ሁሉም የፓርቲው ትንቢተኞች አንድም ሁለትም ናቸውና–"የአያ ነውጤ መንትያ ልጆች" እንዲል አንድ ወዳጄ። …እስቲ በቅድሚያ ዛሬ በህግ ጥላ ስር ካሉት አቶ አንዱዓለም አራጌ እንነሳና ማሳረጊያችንን "…የቦይ ውሃ ናቸው" ተብለው በሌላ ተሰንጣቂ አመራር ወደተዘለፉት የፓርቲው ወረፈኛ መሪ ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ላይ እናድርግ፤የማወጋችሁ አብነታዊ ቅምሻ ብቻ ነውና።…

…በ97 ዓ.ም. ምርጫ ወቅት እኔም ሆንኩ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ አዲስ አበባ ውስጥ በቅንጅቱ ነውጥ አከፋፋይነት ስድስት ቁጥር ማለያ ለብሰው ሲጫወቱ እንደነበሩ የምናውቃቸው የአመፅ አጋፋሪው አቶ አንዱዓለም አራጌ፤ 'በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ መካከለኛው ምስራቅና ሰሜን አሜሪካው ዓይነት ህዝባዊ ማዕበል ካልተነሳ እንትፍ… እንትፍ ከምላሴ ፀጉር ይነቀል' ሲሉ ነበር። ከንግግር አልፈውም በስራ ላይ የተጠመደውን የሀገራችንን ህዝብ ለአመፅ በመቀስቀስ ግልፅ የሆነ ህግ የመፃረር ተግባርን ሲከውኑ ነበር።

ትናንት "ዳግም የአመፅ ስራ አላከናውንም" ብለውና ምህረት ጠይቀው ከእስር ቤት የተለቀቁት አቶ አንዱዓለም ፤ የሚቋምጡለት ነውጥ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ውስት ሊከሰት የሚችልበት ነባራዊ ሁኔታ በሩ የተከረቸመ መሆኑ እንኳን እንዲገባቸው የሚፈልጉ አይደሉም–ዓላማቸው ህገ-መንግስቱን በመጣስ ወደ ስልጣን የሚወስድ ማናቸውንም ዓይነት ሁከት መፍጠር ነበርና። ግና እርሳቸው ምንም ያልሙ ምን፤ ሰውዬው ህገ-መንግስቱን ተመርኩዞ በተረቀቀውና የህዝቡ ወኪል በሆኑት የተወካዩች ምክር ቤት አባላት በከፍተኛ ድምፅ ባፀደቁት የፀረ-ሽብር አዋጅን ተላልፈው በመገኘታቸው እንደ ማንኛውም ዜጋ በሀገራችን ፍርድ ቤቶች ጉዳያቸው ሲታይ ቆይተው የተከሰሱበትን ወንጀል መከላከል ባለመቻላቸው የህግ የበላይነት ተግባራዊ እንዲሆንባቸው ተደርጓል።

በምርጫ 2002 ወቅት ቢጤዎቼ ሲናገሩ እኔም ለምን ይቅርብኝ ብለው ነው መሰል፤ ቅድም እንደነገርኳችሁ በተሰንጣቂ የፓርቲው አባላት "የቦይ ውሃ፣ የቦይ ምንትስ" እየተባሉ ማንነታቸው በየመገናኛ ብዙሃኑ እንደ ጣቃ ሲተረተርላቸው የሰነበቱት ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ እንኳን "የፖለቲካ ፓርቲዎች መዳከም የሰሜን አፍሪካን ዓይነት ህዝባዊ አመፅ ለማነሳት አያግደውም" ማለታቸውን ዛሬ ላይ ሳስበው ድንቅ ይለኛል። ምክንያቱም ተሰንጣቂው የአንድነት አመራር እንዳሉት ዶክተሩ

“የቦይ ውሃ” ስለሆኑ ማንም ወዳሻው የሚነትታቸው ከሆኑ ነገ ደግሞ ሌላ የሰሙትን ነገር አለመናገራቸውን ማንም እርግጠኛ ሊሆን ስለማይችል ነው።

እርግጥ ዶክተሩ በፓርቲው አመራሮች ከወዲያ ወዲህ እንደ ፔንዱለም እየተወዛወዙ አንድነት የተሰኘውን የሁከት ማቀነባበሪያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የነውጥ ተንባዮች ቡድንን እንዴት እንደሚመሩት ለእኔ ግልፅ ባይሆንም፤ አንባቢዎቼ ግን ፓርቲው ተግባሩን ቀይሮ ወደ ትንቢት መናገሪያ ቤተ-መቅደስነት መገንዘባችሁ የሚቀር አይመስለኝም። ለነገሩ የያኔው የዶክተሩ አባባል የፓርቲው አመራሮች በፀረ-ህገ-መንግስታዊ ብረት ድስት ውስጥ ተቀቅለው የበሰሉ መሆናቸውን አፍ አውጥቶ የሚናገር ነው—“ከዝንጀሮ ቆንጆ ማንን ይመርጧል” እንዲል የሀገራችን ሰው፡፡

እንግዲህ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ ቀደም ሲል ከጠቀስኳቸው የአንድነት ፓርቲና የአመራሮቹ ጥቂት አብነታዊ ማንነቶች በመነሳት አንድ ወሳኝ ሃቅን መረዳቱ አይቀርም። ይኸውም ፓርቲውና አመራሮቹ ስልጣንን ያለ ህዝብ ይሁንታ ለማግኘት፣ ከፍ ሲልም ህዝቡን በመናቅና ህገ-መንግስቱን በመጣስ ላይ ተሰማርተው ሲንቀሳቀሱና እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ነው። ይህ ድርጊታቸውም ለይስሙላ ህገ-መንግስቱን አክብረን በሰላማዊ ትግል እንደ ፓርቲ እንሰራለን እያሉ፤ በተነፃፃሪው ጭልጥ ባለ የፀረ-ህገ-መንግስታዊ ባህር ውስጥ መስመጣቸውን ያሳያል—በህገ-መንግስቱ ሽፋን ፀረ-ህገ-መንግስታዊነትን የማቀንቀን አባዜ። እናም ከሰሞነኛው የፓርቲው የተለመደ ሱስ እኔ የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ ‘በህገ-መንግስቱ ሽፋን ፀረ-ህገ-መንግስታዊነትን ማራመድ ይቻላልን?’ የሚል ጥያቄን ለማንሳት እገደዳለሁ።

ምንም እንኳን በአዋጁ ምክንያት ጥቅማቸው የተነካ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች፣ ስልጣንን በውጭ ሃይል ተፅዕኖ ለማግኘት የሚያልሙት አንድንትና ተጣማሪዎቹ የመሳሰሉ ነውጥ ዓላሚዎች እንዲሁም አንዳንድ በዚህ መስመር የተሰለፉ የግል ሚዲያዎች ከዓላማውና ከግቡ ጋር ያልተገናኙ “የፕሬስ ነጻትን የሚያፍን፣ የመናገር ነፃነትን የሚገድብ…ምንትስ” የሚሉ “የዳቦ ስሞች” ቢሰጡትም፤ ሃቁ ግን ህገ-መንግስቱን ተከትለው ህዝቦች በሠላም፣ በነጻነትና በተረጋጋ ሁኔታ ያላቸው ህገ- መንግስታዊ መብት ከመሸርሸር አደጋ እንዲጠበቅ እንዲሁም ሽብርተኝነት ለሀገራችን ሁለንተናዊ ዕድገት ጸር በመሆኑ የህግ አግባብን ተከትሎ ተግባሩን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በማለም የወጣ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህን እኩይ ተግባር ፈጻሚዎችንና አስፈጻሚዎችን እንቅስቃሴ ከጅምሩ ለመቅጨት የአዋጁ አስፈላጊነት አጠያያቂ አይሆንም—ሀገሪቷና ህዝቧ በሽብርተኝነት ዘግናኝ ተግባር ይናጡ ካልተባለ በስተቀር።

ያም ሆነ ይህ እዚህ ላይ ከአንድ አማተር አባሉ በስተቀር በህዝቡ ፍትሐዊ ድምፅ ፓርላማ እንዳይገባ የተቀጣው አንድነት ፓርቲ ‘ህገ-መንግስቱን ተንተርሼ እስከ አንድ ሚሊዮን ህዝብ ፊርማ

አሰባስባለሁ፣ የአዋጁ አንቀፆች ከህገ-መንግስቱ ጋር ይጣረሳሉ እንዲሁም ከፍተኛ አመራሬን አቶ አንዱዓለም አራጌንና የምክር ቤት አባሌን አቶ ናትናኤል መኮንንን አሳጥቶኛል' በማለት በህገ-መንግስቱ ሽፋን በአዋጁ ላይ ስላራመደው ፀረ-ህገ-መንግስታዊ እሳቤ ማውሳት ተገቢ ይሆናል። እስቲ ሁሉንም ልቦለዳዊ ዳንኪራዎች ተራ በተራ እንመልከታቸው።

እርግጥ አንድነት ፓርቲ ፊርማ ማሰባሰብ መብቱ ነው–እንኳንስ አንድ ሚሊዮን ቀርቶ ካስፈለገውም ሰማንያ ሚሊዮኑንም የሀገራችንን ህዝቦች አስፈርማለሁ ማለት ይችላል። ምኞትና ውሸት አይከለከልምና። አስገራሚው ነገር ግን የፓርቲው "ልብ እንቅርትን ይመኛል" ይሉት ዓይነት አስቂኝ ልቦለዱ ነው። በእኔ እምነት አንድነት ፓርቲ የጠቀሰውን ያህል ፊርማ ማሰባሰብ የሚችለው እያንዳንዱን አባሉን ቢያንስ አምስት ሺ ጊዜ በተለያየ ስም ደግሞ ደጋግሞ ካስፈረመ ብቻ ነው። ምክንያቱም ፓርቲን ይህን ያህል ሰው የሚደግፈው ቢሆን ኖሮ በምርጫ 2002 ላይ መድረክ ውስጥ ሆኖ ሲወዳደር (ለዚያውም ተጣምሮ) በቂ የሆነ መራጭ ባገኝ ነበር።

ፓርቲው ግን አብረውት ካሉት የማይተማመኑ "ባልንጀሮቹ" ጋር ኮሮጆው የመራጭ ድምፅ ሲናፍቀው ቀርቷል።..."እንደ ናፈቅሽኝ ቀረሽ" አለ ዘፋኙ።...እናም እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የያኔዎቹ ትንቢት ተናጋሪዎች ቡድን የፊርማ ማሰባሰብ ነገር "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" እንዲሉት ብቻ ይመስለኛል። ለማንኛውም በቀጣዩ ፖረቲው አመራሮች ምን ሊሉ እንደሚችሉ የምንሰማው ጉዳይ ይሆናል–መቼም የውሸት ፈረስ ልጓም የለውምና።

አንድ ተቃዋሚ ፓርቲ ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርግ አመፅ ያለ እየመሰለው ልቡ የሚማልለው እንዲሁም ሰልፍ አድራጊው ለይስሙላ ስለ ህገ-መንግስቱ ሲያነሳ የፀረ-ህገ-መንግስታዊ ካራውን ግራ ጎኑ ላይ ደብቆ በመሻጥ እርሱም በይስሙላዊ ፉክከር እሳቤ 'ህገ-መንግስቱ ተጣሰ' ማለት የሚቀናው አንድነት ፓርቲ፤ በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁ ላይም "ከጳጳሱ ቄሱ" እንዲሉት ዓይነት ሆኖም ለመተወን ፈልጓል– የአዋጁ አንቀፆች ከህገ-መንግስቱ ጋር ይጣረሳሉ የሚል አላዋቂ ዲስኩር በማሰማት። ሃቁ ግን ፓርቲው አዋጁ ለሚፈልገው ዓላማ ምቹ ስላልሆነለት ብቻ በጭፍን ጥላቻ ተነሳስቶ እንደሰጠው ስም አይደለም።

እርግጥ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው በዴሞክራሲያዊ ሀገር ውስጥ አንድ አዋጅም ይሁን ዝርዝር ህጎች የሚወጡት ህገ-መንግስቱን ተንተርሰው ነው። ህገ-መንግስቱን ተፃርረው የሚወጡ አዋጆችም ይሁን ህጎች በምንም መልኩ ተቀባይነት የላቸውም። ከዚህ አኳያ በዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን ወስጥ ባለው የህግ ተወካዩች ምክር ቤት የሀገራችንን ብሔራዊ ደህንነት ለማስጠበቅ ጉዳዩ በሚመለከተው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ለዝርዝር ዕይታ ቀርቦና ተመርምሮ የፀደቀው የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ በምንም መልኩ ከህገ-መንግስቱ ጋር አይጋጭም።

ይህ ማለት ግን አንድ የሆነ ኃይል ከመሬት ተነስቶ የፓርላማው አባላት ይህን ጉዳይ እንደማይመረምሩ አስመስሎ በማቀረብ የፓርላማውን ሰናይ ተግባር በማጠማዘዝ ለራሱ ርካሽ የፖለቲካ ፍጆታ አያውለውም ማለት አይደለም። ምንም እንኳን አንድነት ፓርቲ ያነሳቸውና ከህገ-መንግሰቱ ጋር ተጋጭተዋል የተባሉት የአዋጁ የትኛዎቹ አንቀፆች እንደሆኑ ለእኔ ግልፅ ባይሆንም፤ የሀገርን ብሔራዊ ደህንነት ለማሰጠበቅ ሲባል ግን ህገ-መንግስቱን ተመርኩዞ አስፈላጊ የሆነ ማንኛውም አዋጅ ሊወጣ እንደሚችል ፓርቲው ቢያንስ ለታይታ ቢሆንም የጠቀሰውን ህገ-መንግስት ገላልጦ ማንበብ ያለበት ይመስለኛል–ስለማያውቀው ህገ-መንግስት በደፈናው እያጣቀሰ ከመናገሩ በፊት።

ማንኛውም ሰው በህግ ፊት እኩል እንደመሆኑ መጠን፤ አንድ አዋጅ ወይም ህግ የሚወጣው ለሁሉም ዜጎች ነው–ለፖለቲከኛውም፣ ለሙዚቀኛውም፣ ለመሃንዲሱም፣ ለሀኪሙም፣ ለቀዳሹም፣ ለተኳሹም…ወዘተርፈ። ግና አንድነት ፓርቲ ይህን ዕውነታ እንዳላየ ወይም እንዳልሰማ በማለፍ አሊያም በአላዋቂነት አዋጁ ‘አመራሮቼን ነጥቆብኛል’ ብሏል–በዚህም ምክንያት ህጉ መሰረዝ እንዳለበት በማተት። በእኔ እምነት ይህ የፓርቲው አስገራሚ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ምልከታ ሁለት አንድምታዎች ያሉት ነው። አንደኛው ‘እኛ እንደፈለግን ከህግ ውጪ መሆን እንችላለን’ የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ አዋጁ በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እየገቡ እንዳይፈተፍቱ ያገዳቸውን የአክራሪ ኒዮ-ሊበራሎችን አጀንዳ ተቀብሎ መጮህ ነው።

እደሚታወቀው በህግ ካለተደነገገ በስተቀር በየትኛውም ሀገር ውስጥ የሚኖር ዜጋ የህግ የበላይነትን በመፃረር እንዳሻው ሊኖር አይችልም። የዜጎች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በህግና ስርዓት የሚመራ ካልሆነ የትኛውም ወገን የመኖር ዋስትና ሊኖረው አይችልም። የመኖር ዋስትና በሌለበት ሀገር ውስጥ ደግሞ ሰላምና መረጋጋት ይጠፋና እንደ ሰው ለመንቀሳቀስ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ይደረሳል። መብት ሰጪና ነሺ ጉልበተኞች ይሆናሉ። ጉልበተኞቹም ሌሎች ዜጎችን እንዳሻቸው በማድረግ የባሪያና ሎሌ ስርዓት መፍጠራቸው አይቀሬ ነው። እናም ይህን ሁኔታ ለመከላከልና ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን የህግ የበላይነት መኖር የግድ ይላል። እናም አንድነትም ይሁን የትኛውም ሰላማዊ ፓርቲ ነኝ የሚል የፖለቲካ ክንፍ ህግ ባለበት ሀገር ውስጥ እየተንቀሳቀሰ ከህግ በላይ ሊሆን አይችልም።

ታዲያ እዚህ ላይ አንድነት ፓርቲ አመራሮቹ በተከሰሱበት የሽብርተኝነት ወንጀል ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው ምክንያት በሀገሪቱ ህግ መሰረት በህግ ጥላ ስር ስለዋሉ፤ የግድ ከህግ በላይ ሆኜ ህግን ሽራለሁ ብሎ የመነሳቱ ስህተት ዋነኛ ምክንያት ይኸው ይመስለኛል። ምክንያቱም አመራሮቹ ጥፋተኛ ሆነው የተገኙት በተከሰሱበት የሽብርተኝነት ወንጀል እንጂ በፖለቲከኝነታቸው

ባለመሆኑ ነው። ለነገሩ ሀገራችን ውስጥ የታሰረ ወንጀለኛ እንጂ ፖለቲከኛም ይሁን ጋዜጠኛ የለም።

ያም ሆነ ይህ ግን እርግጥም ፓርቲው ሰዎቹ 'አመራሮቼ ናቸው' የሚል ከሆነ ማደረግ የነበረበት ግለሰቦቹ በወንጀል በተከሰሱበት ወቅት ጥፋተኛ አለመሆናቸውን የሰውና የሰነድ ማስረጃ በማቅረብ በፍርድ ቤት ነፃ ማስባል ነበር። ከዚህ ውጪ ሰዎቹ በፍርድ ቤት በአሳማኝ የሰውና የሰነድ ማሰረጃ ጥፋተኛ ተብለው ካበቁ በኋላ፣ ወንጀላቸውን በመደባበቅ 'አዋጁ አመራሮቼን ስላሳጣኝ በፊርማ አሰርዘዋለሁ' ማለት በየትኛውም መንገድ ተቀባይነት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር፣ 'ህግን ደፍጥጠን እንደፈለገን ብንንቀሳቀስ ማን ከልካይ አለብን!' የማለት ያህል ቢታረም በጄ ነው ባይ ነኝ።

ምንም እንኳን የሀገራችን ተቃዋሚዎች ወጥና የተዘረዘረ መስመርና ፖሊሲ  የሌላቸው መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ቢሆንም፣ በእኔ እምነት አንድነት ፓርቲ ያው እንደ ማንኛውም የተቃውሞ ጎራ ቡድን በቅንጭብጫቢና አጀንዳዎች እየተመራ መሆኑን በዚህ ጉዳይም ላይ ይፋ አድርጓል ባይ ነኝ። አጀንዳው ደግሞ የውጭ ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎችን ፍላጎት ማራመድ ነው። እንደሚታወቀው እንደ አምኒስቲ ኢንተርናሽናል፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች እና ኢንተርናሽናል ክራይስስ ቡድንን የመሳሰሉ ፀረ-ኢትዮጵያ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች አዋጁ ሀገራችን ውስጥ ገብተው በውስጥ ጉዳያችን ላይ እንዳሻቸው ስላደረጋቸው አዋጁን መንግስት እንዲሰርዘው ከፍተኛ የማጥላላት ዘመቻ ከፍተውበት ነበር—ዛሬም ድረስ ቢሆን። ግና ምን ያደርጋል!?...የእነዚህ የርዕዮተ-ዓለም ሰባኪዎች  አሉባልታ ሀገራችን ውስጥ አንዳችም ነገር መፍጠር አልቻለም እንጂ።

እርግጥ ማንም ቢሆን እነዚህን ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች በአዋጁ ላይ ያሰሙት ዲስኩር በውጭ ስላልተሳካላቸው እስቲ በሀገር ውስጥ ደግሞ በአንዳንድ ፓርቲዎች እንሞክረው አለማለታቸውን ማንም እርግጠኛ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም አንድነት ፓርቲ በፊርማ አሰርዛለሁ በማለቱ  በአዋጁ ላይ ያነሳቸው ነጥቦችና የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎቹ ያልተሳካ ዲስኩር ተመሳሳይ ስለሆነብኝ ነው።

ለነገሩ እንዲህ ዓይነቱ የአጀንዳ ቅብብሎሽ በሰላማዊ መንገድ በሚንቀሳቀሱ አንዳንድ የሀገር ውስጥ ተቃዋሚዎችና የራሳቸውን አጀንዳ በሀገራችን ላይ ለማስፈፀም በሚሹ የውጭ ሃይሎች መካከል ትናንትም ይሁን ዛሬ የነበረ ነው። (እዚህ ላይ የዛሬ ሁለት ዓመት ገደማ የመድረክ አመራሮች ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም ለሚያራምደው ሂዩማን ራይትስ ዎች በበሬ ወለደ ተቃዋሚነት 'የኢትዮጵያ መንግስት የእርዳታ እህልን ለፖለቲካ ፍጆታ ያውላል' በማለት የሰጡትንና ኋላ ላይ ሀገራችን ውስጥ ባሉት የልማት አጋር ቡድን "ዳግ" አማካኝነት ተጣርቶ ውሸት መሆኑ የተረጋገጠውን የቅጥፈት ምስክርነት ያስታውሷል!) እናም በአንዳንድ የተቃውሞው ጎራ ቡድኖች

ውስጥ ይህን መሰሉ የውጭ ሃይሎችን አጀንዳ ተቀብሎ የመጮህ ጉዳይ የነበረና ያለ በመሆኑ የሚደንቅ አይደለም። ግና አንድነት ፓርቲ አራዳዎች እንደሚሉት 'የሚያወራው ነገር እንደ ቋምጣ ሲያጥረው' በዚህ መንገድ በመንቀሳቀሱ እኔም ሆንኩ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ በእርሱ ቦታ ሆነን ለማፈር እንገደዳለን—ተግባሩ የኢትዮጵያዊያን ህሊና ፈፅሞ የማይፈቅደው ለባዕዳን መላላክ ነውና።

ያም ሆነ ይህ እስቲ እዚህ ላይ በእነዚህና ቀደም ባሉት ማንነቱ በህገ- መንግስቱ ሽፋን ፀረ-ህገ-መንግስታዊነትን በማቀንቀን የምናውቀው ፓርቲው 'ዕውን የፀረ-ሽብር አዋጁን እርስ በእርሱ በመፈራረም የመሰረዝ፣ ከፍ ሲልም እርሱ የመረጠውን አዋጅ የማፅደቅ መብት አለውን?' የሚል ጥያቄ እናንሳ። ፓርቲው "በልጅ አመካኝቶ..." እንደሚባለው በሌለ እምነቱ እየደጋገመ የሚጠቅሰው የኢፌዴሪ ህገ-መንግስት ፤ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዚህ ህገ-መንግስት መሰረት ለፌዴራሉ መንግስት በተሰጠው የስልጣን ክልል ህጎችን እንደሚያወጣ በግልፅ ይደነግጋል። የመሻር መብት እንዳለውም ጭምር።...እንግዲህ ይህ የሀገራችን ህገ-መንግስት የሚያዘው ነው።

ጉደኛው አንድነት ፓርቲ ደግሞ ምናልባትም 'ሁላችንም አንድ ዓይነት አስተሳሰብ ስላለን ልክ በህግ ጥላ ስር እንጋሉት አመራሮቻችን በቀጣይነት እኛንም ያሰጋናል' በሚመስል መንፈስ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን አባላት በመተካት ህግን መሰረዝ አለብኝ እያለ ነው። ኧረ እንዲያውም በዚህ አያያዙ ህጉን 'እኔ እራሴ አወጣዋለሁ' ሳይል የሚቀር አይመስለኝም። እናም ፓርቲው በዚህ ቀቢፀ-ተስፋው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰፈረውን ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌ በመፃረር ህገ-መንግስቱን በገሃድ እየናደው ነው። ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ በአንድ በኩል በህገ-መንግሰቱ ጥላ ስር ነኝ እያሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ግልፅ የሆነ ህገ-መንግስታዊ ጥሰት ተቀባይነት እንደሌለው ማወቅ ያለበት ይመስለኛል—ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ሁለት ዛፍ ላይ አይወጣምና። አዎ! በአንዴ ሁለት የማይገናኙ ፅንፎችን መምረጥ አይቻልም። አንዱን ፅንፍ የግድ መምረጥ ያስፈልጋል።

አንድን አጀንዳ በመምዘዝ አሊያም በመቀበል ህገ-መንግስታዊነትንና ፀረ-ህገ-መንግስታዊነትን በአንዴ እያጣቀሱ መጓዝ የሚቻልበት ወቅት ጊዜው ያለፈበት አሮጌ እሳቤ ነው። እናም አያስኬድም። ስለሆነም አንድነት ፓርቲ በህገ-መንግስቱ መሰረት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዝርዝር ታይቶና ታምኖበት ስራ ላይ የዋለውን የፀረ-ሽብር አዋጁን ሊያውቀው የማይፈልገውን ህገ-መንግስት እየጠቀሰ 'ከህገ-መንግስቱ ጋር ይፃረራል' ከማለት ይልቅ፤ ራሱ እየፈጠረ ያለውንና ለሰሚው ግራ የሆነውን ግልፅ ህገ-መንግስታዊ ጥሰት ማቆም ያለበት ይመስለኛል። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ለህዝብ ጥቅም ተብሎ የፀደቀውን የፀረ-ሽብርተኝነትን አዋጅ መቃወም ተቃራኒውን መናፈቅ ነው—ሽብርተኝነትን። እናም የፀረ-ሽብርተኝነት ህጉን የሚፃረሩ

ሽብርተኝነትን የሚናፍቁ ህገ-ወጦች መሆናቸውን ቆም ብሎ በማሰብ መገንዘብ የሚገባ ይመስለኛል። አበቃሁ።